# "ኦሮሚያ" የማን ፍልሰማ ቁቢስ (የላቲን ፊደል) ?

# ክፍል ፩

## መግቢያ

በዚህ ጥናታዊ ጽሑፍ "የኦሮሚያ" ፈጠራ በማን፣ መቼና እንዴት እንደሆነ ይዘረዘራል። በ19ኛው ክፍለ ዘመን ምዕራብ አውሮፓውያን የአፍሪቃን አህጉር እንደ ቅርጫያ ሥጋ ለመቀራመት ሲጣደፉ ለዚህም ተግባራቸው አስቀድመው ሰላዩችና መንገድ ጠቋሚዎችን በኮተሊክና ፕሮቴስታንት ክርስቲያን ተብዬ የወንጌል መልእክተኛነት ስምና ሽፋን "አውሬና አረመኔ የጥቁር ሕዝብ መኖሪያና ጨለማ አህጉር" ብለው የሚጠሩትን ቅኝ ግዛት ለማደርግ የፈጸሙት በአጭሩ ይቀርባል።
የምዕራብ አውሮፓ ቅኝ ገዥ ተስፋፊዎች፣ ዘረኞችና አረመኔዎች የክርስትና ጩንበል አጥልቀው የኢትዩጳያን ጥንታዊ ነፃ አገርነትና ኦርቶዶክስ ሃይማኖት አጥፍተው የአነሱ ተገዥና መስፈሪያ እንደ አሜሪካ፣ አውስትራሊያ፤ ደቡብና ምሥራቅ አፍሪቃ ለማስደረግ ያልፈነቀሉት ድንጋይ ከቶ እንዳልነበረ በአጽንኦት ይሰመርበታል። በ16ኛው ክፍለ ዘመን የመጀመሪያው አጋማሽ ላይ የኦስማን ቱርክኛ አረብ ቅጥረኛው በነበረው ግራኝ አሕመድ አልጋዚ ጅሃዳዊ የ14 ዓመታት ወረራን ለመከላከል ርዳታ የመጡት የፖርቱጋልና እስፓኝ ኮተሌኮች ከድሉ ማግስት የኢትዩጵያን ኦርቶዶስ የአሌክሳንደርያ ሐዋሪያዊው መንበረ ማርቆስ ርቱዕ ሃይማኖት አስጠፍተው የሮማውያን መጢቃ ሕዝቦች የቫቲካን ኮተሊካዊት ተብዬ መናጆ ጥገኛ ለማድረግ የሸረቡት ሴሬ ባይሳካም እንኳን አገራችን በነዚህ አወናባጆች ምክንያት ለሰላሳ ዓመት ያህል ስትታመስ መቆየቷ፤ ብዙ ንብረትና ሕይወት መውደሙም ይታሰባል።

የሴማውያን ቋንቋ ምሁር የነበረው ጀርመናዊው ኢዩብ ሉዶልፍ መለውን ጥቁር አፍሪቃ በጠቅላላ <u>ፕሮቲስታንት</u> ለማድረግ በኢትዩጵያ በኩል ሊያመች ይቻላል ሲል ባቀረበው ሃሳብ መሠረት፣ የ19ኛው ክፍለ ዘመን የጀርመንና ሲዊድን ፀረ ማሪያሞች ለእንግሊዝ የሚሲዎን ማኅበር ተቀጣሪ በመሆን እ.አ.አ በየካቲት ወር 1830 ዓ.ም እነ ሳሙኤል ጎባትና ክርስቲያን ኩግለር የተባሉት ወደ ኢትዩጵያ መጥተው በትግሬ ክፍለ አገር አዴግራት ላይ ከደጃዝማች ሰባጋዲስ ዘንድ ቀርበዋል። ከዚያም ጊዜ ጀምሮ በተከታታይ የኮተሊኮችና የፕሮቴስታንት ሚሲዎኖች ተባብረው፣ አልፈው ተርፈውም ከተሰፋፊው እስላማዊው እስማኤል ፓሻ የግብፅ ገዥና የቅኝ ግዥ ተስፋፊዎች እንግሊዞች ዋና ደላላና ጥገኛ መንግሥት ጋራ ወግነው ፀረ ኢትዩጵያ ዘመቻና ሴራ መጎንጎናቸው በበቂ ማስረጃ ይቀርባል። ለምሳሌ በአጤ ዩሐንስ ፬ኛ ዘመነ መንግሥት ሚሲዎን ተብዬዎቹ እነ ፍላድ፣ ዩሐን ክራፍ፤ ሙዝንጅርና ጎባት አበሻን ማዋረድና ማሳፈር፣ ምድሩን ከፋፍሎ መያዝ፣ የቀይ ባሕርን ዳርቻንና የአውሳን ጨው ማዕድን ስፍራዎችን በእንግሊዝ፣ በፈረንሳይና በግብፅ ወታደራዊ ኃይል እንዲያዙ ለማድረግ በጣም ሰፊ ቅስቀሳና ውትወታ ማድረጋቸውን የታሪክ ሰንድ ያስረዳል። የምፅዋ የግብፁ እስማኤል ፓሻ እንደራሴ የነበረው የስዊዘርላድ ፈረንሳዊ ዘርያ ሙዚንጅር፣ የጀርመናዊው ክራፍ የልብ ጓደኛ ለፀረ አበሻ ዘመቻው የስለላ ጉዞ ሲያደርግ አውሳ ላይ ጀግናው የአፋር ኢትዩጵያዊ ሕዝብ ከነመላ ጓዙና ቡድኑ ጋራ ደምስሶታል። የፕሮቴስታንቶ "ሚሲዎኖቹ" እነ ክራፍና ተከታዩቹ ለጋላ ነገድ ከኢትዩጵያውያን ይበልጥ ዋና አሳቢ መስለው ያለማቋረጥ በሃይማኖት ሽፋን የሚያናፍሱትን ጥላቻና ጠባብ የጎሣ ስሜት ቅስቀሳ ከሥር መሠረቱ በዚህ ጽሕፍ ይገለጻል።

<u>"ኦሮሚያ</u>" ጀርመናዊው ዩሃን ክራፍ ለመጀመሪያ ጊዜ ከፈጠረው <u>"ኦርማኒያ</u>" ያጠራር ስያሜ መገኘቱን፤ የጋልኛ ወይም የወሮሞኛ ልሳን በላቲን የቁቢ ፊደል እንዲጻፍ የመጀመሪያውን ሃሳብ አፍላቂ እሱው ራሱ መሆኑ ይገለጻል። ቀጥሎም የመኢሶን ድርጅት መሪና የወታደራዊ ደርግ የሶሻሊዝም አስተማሪ የነበረው ዶክተር ኃይሌ ፊዳ በጀርመን ሃምቡርግና በፈረንሳይ ቆይታው አዘጋጅቶ በሚስጥር ያሰራጨውን ወታደራዊ ደርግ አገር አጥፍቶ እ.አ.አ 1991 ዓም ሲጠፉ ቁቢ በዘመነ ወያኔና ኦነግ ተግባራዊ ሆኗል። የፕሮቲስታንት ሚሲዎኖች በአንድ በኩል ለኦሮሚያ የፈጠራ ክልል ነፃ ሪፑብሊክነት፣ በሌላ በኩልም የኢትዩጵያን ባሕልና ይልቁንም ኦርቶዶክስ ሃይማኖት ለማስለወጥ ተመኝተውና አስበው በጣም ከፍተኛ ያላቋረጥ ዘመቻ እያደረጉ ዘወትር የሚያስነዙት ፀረ አበሻ ፀረ-ኦርቶዶክስ፣ ፀረ-ሴማዊ የሥነ ልቡና ጦርነት ሁኔታ በሰፊው ይቃኛል። እራሳቸውን ኦረሞ ብለው የሚጠሩት ጠባብ የጋላ ጎሠኞችና የባሕር ማዶ ጠባቂዎቻቸው ለምን ፀረ-ዐማራ ቅስቀሳና የኢትዩጵያን ጥቁር ሕዝብ ነፃ መንግሥት የአያሌ ሽህ ዘመናት ታሪክና ሥልጣኔ እንደሚክዱ፣ ዐማራውን ማኅበረሰብ ከሌላ አህጉር እንደመጣ "ቅኝ ግዥ" አስመስለው የሚቀዣብሩትን የታሪክ ክለሳና ብረዛ በሰፊው ይቃኛል።

የጋላ ነገድ ከግራኝ አሕመድ ወረራ በኋላ ከደቡብ ምሥራቅ ኬንያ ቦረና ከሸበሌና ጁባ ሸለቆዎችና ከቤናዲር በሱማሌ ዘላን ነገዶች የተባረሩት ሁለቱ የቦረናና በርቱማ የጋላ ጎሣዎች በኢትዩጵያ ምድር ጥንታዊ ከባሌ እስከ ትግሬ፤ ከዘይላ እስከ ቢዛሞ (ወለጋ( ድረስ በተከታታይ ወረራና ዝርፊያ የቅርብ ዘመን መጤ ሠፋሪዎች መሆናቸው ተሸፍጦ ነባር እንደሆኑ ተደርጎ የሚለፈፈው የውሸት ፕሮፓጋንዳ ይጋለጣል። ጥንታዊው ነባር የኢትዩጵያ ሕዝብ ዐማራው፤ ጉራጌው፤ ሃድያው፣ ከምባታው፣ ወላሞው፣ ጋሞው፣ እናሪያው፤ ትግሬው፤ አገው፤ ወዘተ. በደቡብ፣ በምዕራብና በምሥራቅ ኢትዩጵያ በጣም ሰፊና ለምለም መሬቱን በሉባ የጋለ ወራሪ ጦር ከባሌ እስክ ትግሬ ተወሮ መያዙን፣ ሸዋዎችም ይህንኑ የጥንት አገራቸውን ለማስመለስ ከ፲ኛው ክፍለ

ዘመን ጀምሮ በተከታታይ የደረጉት ያላቋረጠ ትግል በዘመነ ዳግማዊ አጤ ምንይልክ መሪነት የተፈጸመውን ተገቢ ዘመቻ እንበለ እፍረት የወረሞ ጠባብ ጎሠኞችና የባሕር ማዶ ሞግዚቶቻቸው የአፍሪቃ ቅኝገዥ ተስፋፊዎችና ተቀራማቾቹ ከእነ እንግሊዝ፣ ስፓኝ፤ ፖርቱጋል፤ ፈረንሳይና ጣሊያን ጋራ አመሳስለው የሚያነበንቡበት ማወናበጃ ይጋለጣል

በኢትዮጵያ የባሪያ ነጋዴዎች እነማን እንደነበሩና በባርያ ንግድ ስም በኢትዮጵያ ሕልውና ላይ የምዕራባውያን ዘመቻና የደቡብ ኢትዮጵያ ሕዝብ ሰቆቃ ይዘገባል። ከጥንት ሸዋ ግዛት በስተደቡብና ምዕራብ የሚገኙት ለምለም ክፍለ ሀገራት ሁሉ ለፕሮቲስታንት ፈረንጆች መስፈሪያነት በጣም ተስማሚ እንደ አውስትራሊያ፤ ኒውዚላንድ፤ አሜሪካና ምሥራቅና ደቡብ አፍሪቃ የታለሙ እንደነበረም ማስረጃው ይቀርባል።

# <u>የካቶሊክና ፕሮቴስታንት ሚሲዮኖች ተልዕኮ ከትናንት እስከ ዛሬ</u>

በ16ኛው ክፍለ ዘመን የካቶሊክ ሃይማኖት ተከታይ የነበሩት ቄሶች ቤተክርስቲያኗ አንዳንድ ማሻሻያ እንድታደርግ በሰሜን ምዕራብ አውሮፓ እንቅስቃሴ ጀመሩ። የእንቅስቃሴው መሪዎች ብዙ ቄሶችና መነኩሴዎች ቢሆኑም ከሁሉም የታወቀው የጀርመን ተውላጅ ማርቲን ሉተር (1483-1546) ነው። እንደ ፈረንሳይና እንግሊዝ ማዕከላዊ መንግሥት ያልነበራቸው ጀርመኖች በደረሰባቸው የማንነት ቀውስና በተከተለውም የጀርመን ብሔረተኛነት ስሜት ምክንያት ከሮማው ካቶሊክ መሪነት ተገንጥለው እራሳቸውን <u>ፕሮቴስታንት</u> (Protestant Reformation) የተሃድሶ ንቅናቄ ብለው ሲሰይሙ በአንጻሩ ለሮማ ቫቲካን ካቶሊካዊት ሃይማኖት ታማኝ ከነበሩት ጀርመኖች ጋራ ለ30 ዓመታት የዘለቀ የሃይማኖት ጦርነት አድርገዋል። በነገራችን ላይ በኮተሊኮችና ፕሮቴስታን ተብዬዎቹ መካከል የነገረ መለኮት ልዩነት የለም። የሥልጣን ሽሚያ እንጂ። የሮማ ካቶሊክና ተገንጣይ ፕሮቲስታንቶች የክርስቶስን ባሕርይ በሚመለከት በመጀመሪያ በነቂአ በ325 ዓም፣ በ381 በቆስጠንጥንያ ወዘተረፈ የጸደቀውን የእምነት መሠረት ማላትም <u>መንፈስ ቅዱስ ከአብ ይተላለፋል</u> ተብሎ የፀደቀውን ካቶሊኮች እንዲሁም ከወልድ የሚለውን ጨምረው ከኦርቶዶክስ ርቱዕ ሃይማኖት ተለይተዋል። የሮማ ካቶሊኮች እየሩሳሌምን ከእስላሞች ነፃ እናወጣልን ብለው የመስቀል ጦርነት ዘመቻ በ1204 ዓ.ም ሲጀምሩ የካቶሊካውያን ጦረኞቹ በመጀመሪያ የወረሩትና የዘረፉት የኦርቶዶክስ ዋና መዲና ግሪክ ተናጋሪ የነበረችውን የቆስጠንጥንያን (ኢስታንቡል) ከተማ ነበር።
የሮማ ካቶሊክና ፕሮቴስታንት የተለያዩት በሥልጣን ሹክቻ ነው። የሰሜን አውሮፓ ያልተቀያየጠ ንጹሕ አረመኔ ጀርመን ዘርያዎች በጣሊያን ቅይጥይጥ ወገን አይገዛም በሚል ውስጠ ወይራ ነው። የፕሮቴስታንት የተቃውሞ እንቅስቃሴ የተጀመረውና የተካሄደው በተለያዩ አገሮችና ደብሮች በመሆኑ ምክንያት አንድ ወጥ ሳይሆን እንደየ አገሩ በብዙት የተለያየ ነው። ለምሳሌ ባብቲስት፣ ሉተራን፣ ፕርስቤትሪያን፣ ኮንግሪሽኒስት፣ መኖናይት ወዘተረፈ
ትልቁ የማርቲን ሉተር ሙያ መጽሐፍ ቅዱስን ከሮማይስጥ ወደ ጀርመንኛ ቋንቋ መተርጎሙ ነው። እስከ 18ኛው ምዕተ ዓመት መዳረሻ ድረስ የሮማ ካቶሊክ እምነት ተከታዮች ቤተክርስቲያናቸው ከፈቀደችው ትርጉሞች ሌላ መጸሐፍ ቅዱስ ፓፓውን ሳያስፈቅዱ ማንበብ አይችሉም ነበር።

የሉተር ደቀ መዝሙሮች ኋላ የመጣ ዓይን አወጣ እንዲሉ መጽሐፍ ቅዱስን እንደፈለጋቸው እየበረዙና እየከለሱ በመተርጎም የነሱን የበላይነት ስሜት በየቦታው ለማሰራጨት ሲቃዘኑ ወደ ኢትዮጵያም መዝለቃቸው አልቀረም። ታዲያ! ምጥ ለናቷ አስተማረች እንዲሉ የጀርመንና ስዊድን ክርስቲያን ተብዬዎች በ16ኛው ክፍለ ዘመን የተረጎሙትን መጸሐፍ ቅዱስ ለጥንት የኢትዮጵውያ ኦርቶዶክሳውያን ክርሲትያኖች ሊሰብኩ እጅግ በጣም ተንጠራርተዋል። እንበለ እፍረት የመጽሐፍ ቅዱስ ክለሳና ብረዛውን ዛሬም በሲፌው ተያይዘውታል። በሃይማኖት ስም ግጭትና ጦርነት፣ ባሪያ ንግድ፣ አፓርታይድ ዘረኝነትና ጭቆና የፈጸሙት የሌላውን እምነት፣ ባሕልና ታሪክ ለማጉደፍ የማያደርጉት መቅበዝበዝ ከቶ የለም። የምዕራባውያን የኮተሊክና ፕሮቴስታንት "ክርስትና" ሃይማኖት በአውሮፓና አሜሪካ በአሁኑ ወቅት በከፍተኛ ክስረት ላይ ይገኛል። በያለበት አቢያተ ክርስቲያን ወደ ቤተ መዝክርነትና ንግድ ቤትነት በመለወጥ ላይ ናቸው። ሌላው ትልቁ ጉድና ቅሌት ሕፃናትን የሚያሽረሙጡት የኮተሊክና የፕሮቴስታንት ቄሶችም በያለበት በተለይም በአሜሪካ፣ በአውስትራሊያን አውሮፓ ተጋልጠዋል። እጥፍቶ ለመጥፋት አስብውና ተመኝተው የኢትዮጵያን ጥንታዊ ርቱዕ ኦርቶዶክስ ተዋህዶ ቤተክርስቲያን ያሳማዎችና የግብረ ሰዶማውያን ፍናፍንቶች መፈንጭያ ተገዥ ለማድረግ እንዳበደ ውሻ ይቅነዝነዛሉ። ይህ ዘመቻ በኢትዮጵያ ብቻ አይደለም። ታላቁን የግሪክ ኦርቶዶክሳውያን መነኮሳት ጥንታዊ ገዳም አባቶችን እምነት ለማስጠፋት ከሦስት ዓመት በፊት ጀምሮ ታላቅ ዘመቻ ይደረግባቸዋል። በመስኮብ፣ በሰርቢያና ሌሎች ምሥራቅ ኦርቶዶክሳውያን ላይም ግልጽና ይፋ ወረራ በመደረግ ላይ ነው።

ማርቲን ሉተር የኮተሊክ መነኩሴ ሆኖ ከቆየ በኋላ ከቫቲካን ጣሊያኖች ጋራ በጥቅም ግጭት ሲጣላ ቆቡን ጥሎ ሚስት አግብቶ የተደላደለ ኑሮውን መሥርቶ ብዙ ልጆች ወልዷል። በመጀመሪያ ወደ ኢትዮጵያ የገባው የሉተር ተከታይ የሰሜን ጀርመን ሉቤክ ተወላጅ የሆነው ሄይሊንግ ወይም ጴጥሮስ ኖሊንግ ይባላል። ይህ ሰው ሦስት ዓመታት በፓሪስ ቆይቶ በማልታ በኩል አድርጎ ካይሮ ምድረ ግብጽ ገብቶ ገዳም ውስጥ ከሰነበተ በኋላ እ.አ.አ 1635 ዓ.ም አቡነ

ማርቆስን ተከትሎ አጤ ፋሲል ዘንድ ቀረበ። ሐኪም ነኝ ብሎ ለ14 ዓመታት ያህል በጎንደር ከተማ ኖረ። እጅግ ብዙ ሃብት አከማችቷል። ውሎ አድሮም ፕሮቴስታንትነት ለመስበክ ሲጀምር ታስሮ ከአገር ተባሯል። ወደ ሱዋኪን ማለት የዛሬዋ የሱዳን ወደብ ሲጓዝ ቱርኮች ለሃብቱ ሲሉ ገድለውታል። (E.Van Donzel; Foreign Relations of Ethiopia 1642-1700, ( Holand: 1979), pp.1-2,99)

ጴጥሮስ የዮሐንስ ወንጌልን ወደ ዐማርኛ ተርጉሟል። በዚያን ዘመን በጎንደር የነበረውን የካቶሊኮችን ኃይለኛ ጥላቻ ተጠቅሞ የሉተርን ስብከት ለማስፋፋት ከጅሎ ከሸፈበት።

የእንግሊዝ ቤተ ክርስቲያን ማኅበር (Church missionary Society (CMS)) እ.አ.አ 1799 ዓ.ም ተመሥርቶ ፕሮቴስታንትነትን በእንግሊዝና በዓለም ለማስፋፋት ሥራውን ጀመሯል። ከማኅበሩ ተቀጣሪዎች ብዙዎቹ የጀርመንና የስዊድን ተወላጆች ይገኙበታል።

ቀደም ብሎ በመግቢያው ላይ በተጠቀሰው ወርና ዘመን ፕሮቴስታንቶቹ የስዊዝ ዜጋ የጀርመን ዘርያ የነበረው ሳሙኤል ጎባትና ጀርመናዊው ክርስቲያን ኩግለር ከየሩሳሌም ምድረ ግብጽ ወርደው ከሰነበቱ በኃላ ተልዕኳቸውን ቀጥለው በታህሣሥ ወር እ.አ.አ 1829 ምፅዋ ገብተዋል። ከምፅዋ ወደ አዲግራት ተጉዘው በየካቲት ወር 1830 ዓ.ም ከደጃዝማች ሰባጋዲስ ዘንድ ቀረቡ። ጉዟቸውን ቀጥለው ከሰሜኑ ገዥ ራስ ውቤ ጋራ አድዋ ላይ ተገናኝተዋል። አቶ ኩግለር በመጣ ባመቱ ሞተ። ጎባት ግን በጎንደርንና ትግሬ እይተዘዋወረ የኦርቶዶክስ ሃይማኖትን ዕምነት ለማስለወጥ ያላደረገው ሴራና ውዥንብር አልነበረም። ሆኖም ግን አልተሳካለትም። በመጨረሻም በጠና ታሞ ወደመጣበት ተመለሰ። ቀጥሎም ቻርለስ ኢዘንበርግ የተባለው የሚቴ ኩግለር ተተኪና የጎባት ተወካይ መጣ። እሱም አስቀድሞ ዘጠኝ ዓመት ዝግጅት በባዝል፣ በበርሊንና ለንደን አድርጎ እ.አ.አ በ1833 ዓ.ም ካይሮ ግብፅ ደርሶ በዚያም ተጨማሪ አንድ ዓመት ተመንፈቅ ያህል ዐማርኛና አረቢ አጥንቶ ወደ ኢትዮጵያ ገብቷል።

በ1837 ዓ.ም የቩርተምበርግ ተወላጅ የነበረው ዩሐን ክራፍ የባዝል ሚሲዎን ኮሌጅ ምሩቅ፣ ለእንግሊዝ ሚሲዎን ማኅብር ተቀጣሪ ሆኖ ወደ ኢትዮጵያ በታህሣሥ ወር 1837ዓ.ም መጥቶ በትግሬ አድዋ ከወገኖቹ ከኢዘንበርግና ብሉምሃርደት ጋራ ተገናኝቶ በእነዚህም አማካይነት ራስ ውቤ ፊት ቀርቧል። ክራፍ ራስ ውቤ በመልካም ሁኔታ እንደተቀበሉት ነገር ግን የትግሬ ቀሳውስትና ሕዝብ ክርስቲያን የፕሮቴስታንት ሚሲውኖችን እንደሚጠሉ በሰፊው መዝግቧል። በአድዋ የፕሮቴስታንት ሚሲዎን ማዕከል ለመሥራት የቤቱን መሠረት በመቆፈር ላይ እያሉ ተባረዋል። የተባረሩበትንም ምክንያት ክራፍ እንደገለጸው የሁለቱ ካቶሊክ ፈረንሳዮች የነዳባዲ መምጣትና ከራስ ውቤ ጋር በማበራቸው ምክንያት ነው ብሏል። በመጋቢት ወር 1839 ዓ.ም ጠረ ማርያሞች ከአድዋ ከተማ ሲባረሩ ምፅዋ ገቡ። ኢዘንበርግና ብሉምሃርድ ወደ ካይሮ ሲጓዙ ክራፍ ወደ ሸዋ ለመሄድ ስያመንታ ሰንብቶ ስለታመመ አቅጣጭያውን ቀይሮ ወደ ካይሮ ሄዶ ተቀላቀላቸው። ቀጥሎም ኢዘንበርግና ክራፍ ከካይሮ ተነስተው በግንቦት ወር 1839 ዓ.ም በታጁራ በኩል ሸዋ ግዛት ገብተው ከንጉሥ ሣህለ ሥላሴ (1813-1847) ጋር አንጎለላ ላይ ተገናኙተዋል። ኢዘንበርግ የሚፈልገውን የስለላ መረጃ ሰብስቦ በተመሳሳዩ ዓመት ህዳር ወር ወደ ተላከበት እንግሊዝ ከተመለሰ በኋላ ያማርኛ-እንግሊዘኛ፤ የእንግሊዘኛ-ዐማርኛ መዝገበ ቃላት አሳትሟል። ክራፍ ግን በሸዋ ለሦስት ዓመታት ያህል ቆይቶ እ.አ.አ 1842 ዓ.ም ከሸዋ ግዛት በመሓል አገር በወሎና ትግሬ አድርጎ ወደ ምጽዋ በመሄድ ወደ አገሩ ተመልሷል። በጎንደርና ትግሬ ቀጥሎም በሺዋ በአጠቃላይ ለአምስት ዓመታት ያህል ቆይቶ ከተመለሰ በኋላ ዳግመኛ ወደ ኢትውጵያ ተመልሶ ሸዋን ዋና ምሽጉ በማድረግ መላውን አፍሪቃ ፕሮቴስታንት ለማድረግ በተለይም አሕዛቦች ወይም አእዋሚያን ጋሎችን "ክርስትና ለማንሳት" በከምባታ፣ በእናሪያ፣ በወላሞ ወዘተ. በአረመኔዎች የተከበቡ ክርስቲያኖችን የፕሮቲስታንት ወንጌል ለመስበክ የወጠነው እቅድ ውሃ በላው። በ1842 ዓ.ም ከታጁራ ወደ ሺዋ ምድር እንዳይገባ በሸዋው ንጉሥ ሣህለ ሥላሴ ተከለከለ። ዳግመኛ በምፅዋ በኩል ወደ ትግሬ በሚቀጥለው ዓመት ከግንቦት እስከ ሰኔ ሞክሮ ስለአልሆነለት ጉዞውን ወደ ምሥራቅ አፍሪቃ ዛንዚባር አምርቶከ ሱልጣኑ ሰይድ ሰይድ ጋራ ተወዳጅቶ በ1844 ዓ.ም መኖሪያውን ሞምባሳ ላይ አድርጎ ጋሎችን ከበስተደቡብ በኩል ለማግኘት በተባለ ሰበብ መላውን ምሥራቅ አፍሪቃን ለጀርመንና እንግሊዝ ቅኝ ሠፋሪዎች ቀዳሚ መንገድ ጠራጊ እንደሆነ ይታወቃል። ዘመነ መሳፍንት አክትሞ የኢትዮጵያ አንድነት በአፄ ቴዎድሮስ ሲጀመርና ከእንግሊዞች ጋራ በተደረገው ጦርነት ክራፍ የጀነራል ናፒር የመቅደላ ዘመቻ ሰላይና አማካሪና አስተርጓሚ ሆኖ አገልግሏል። የግብፁ ገዥ እስማኤል ፓሻና የእንግሊዝ ሠራዊት ኢትዮጵያን ወረው እንዲይዙ ዋና አማካሪና ጎትጓች ነበር። በጠቅላላው የፕሮቴስታንት ሚሲዮን ሰላዮች እነ ዩሐን ክራፍ፣ ማርቲን ፍላድ፣ ሳሙኤል ጎባት ወዘተረፈ ሁሉም በኢትዮጵያ የተመኙትና ያቀዱት ሁሉ ባለመሳካቱ በከፍተኛ ቂም በቀል ተነሳስተው የኢትዮጵያን ኦርቶዶክስ ተዋህዶ ቤተ

ክርስቲያን ሃይማኖትና ቀሳውስት አንቋሽዋል። ፀረ ጥቁር ጥላቻና ዘረኝነት አቀንቅነዋል፤ የባሪያ ንግድ ልዩ ተቆርቋሪ መስለው አላዝነዋል።

ከግራኝ ወረራ በኋላ የመጡት የፖርቱጋልና እስፓኝ ኢየሱሳውያን ክርስቲያን ተብዬ ዘረኞች በፈጠሩት ቀውስ የተነሣ ከኢትዮጵያ ሲባረሩ ዘወትር ፀረ-አበሻ ጥላቻና ቅስቀሳ በሰፊው ማጠንጠንና መርጨት እንደጀመሩት ሁሉ ክራፍና መሰሎቹ ሁሉ ወደ ኢትዮጵያ ዳግም እንዳይገቡና ድርሽም እንዳይሉ ስለተከለከሉ ለበቀል ብለው የባሪያ ንግድ በአበሻ አገር፣ በሺዋ እያለ ይልቁንም ንጉሥ ሣህለ ሥላሴን ዋና የባሪያ ነጋዴ አስመስለው ሰፊ የውሸትና የፈጠራ ወሬያቸውን በመላው አውሮፓ ነዝተዋል። በተለይም የቀበሮ ባሕታዊው ዩሓን ክራፍ ያበሻ ሕዝብ ጥላቻ ከቶ ለከትና ገደብ አልነበረውም።
የክራፍ ለጋላ አእዋሚ ነገዶች "ልዩ ፍቅር" ምክንያቱ ምን ነበር? ክራፍ በራሱ ቃል ያለው፤
"During my residence in Shoa I paid particular attention, as I consider them destined by Providence after their conversion to christianity to attain the importance and fulfil the mission which Heaven has pointed out to the Germans in Europe." (J.Lewis Krapf; Travels, Researches and Missionary Labour During an eighteen years Residence... ( London :1968 ) , 2nd ed. P 72)
ባማርኛ ሲመለስ፣

በሸዋ ቆይታዬ ለጋሎች የተለየ ትኩረት ያደረግሁት በእግዚአብሔር ፀጋ ፕሮቲስታንትነትን ከተቀበሉ በኃላ የሠራዊት ጌታ ለጀርመኖች በአውሮጳ ላሳየው የተልዕኮ መሳካት የተመረጡ እንደሚሆኑ በመገመት ነው።
ክራፍ ዋና መመሪያውን ቀጥሎ እንደለው አመልክቷል።

" As the Romanist missionary said, " Give us China and Asia is ours;" so may we say, " Give us Gallas and central Africa is ours"  " (ያው ገጽ 25)

የሮማ ኮተሊክ ሚሲዎናዊ "ሽንን (ቻይናን) ስጡን እሲያ የኛ ትሆናለች" እንዳለው ሁሉ "ጋሎችን ስጡን ማዕከላዊ አፍሪቃ የኛ ይሆናል" ማለት ይቻላል።
ዩሐን ክራፍ ሃሳቡን ሲቀጥል፤

" In my opinion the great advantage to be derived from the succes of this schem will not be so much in the aquisitions which commerce may drive from the Red sea and countries on its shores, as in the extension of European politity and civilization to Arabia, Abessinia, and the whole of South-Eastern Africa. It will weaken Mohamedanism in the land of its birth, Arabia, and on the African coast; tend to supress the Arabian slave-trade, and subjugate East African Heathensim by christianity and its civilisation; and finally open immense and noble regions in Southern Abessinia and among the Gallas to thousands of European emmigrants when America; Australia and Tasmania cease to attract them." ( ያው ገጽ 15)
ያማርኛው ትርጉም፣

<<በኔ ግምት የዕቅዱ መሳካት ጥቅም በቀይ ባሕር ዳርቻ የሚገኙትን አገሮች ንግድ መቆጣጠሪያ ማግኘት ብቻ ሳይሆን የአውሮጳን የፖለቲካ የበላይነትና ሥልጣኔ በአረቢያ፤ በአበሻና መላው ደቡብ ምሥራቅ አፍሪቃ ማስፋፋት ነው።ይህም እስልምናን ከትውልድ ቦታው አረቢያና የአፍሪቃ ጠረፎች ያዳክመዋል፤ ያረቦችን ባሪያ ንግድ ይቀነሳል፤ የምሥራቅ አፍሪቃ አረመኔነት በክርስትናና ሥልጣኔው ይዋጋል፤ ከአበሻ በስተደቡብ በጋሎች መካክል ያለው ውብ ስፍራ ለሽህ አውሮጳውያን ሠፋሪዎች አሜሪካ፣ አውስትራሊያና ታስማኒያ ሳቢነታቸው ሲያበቃ ሰፊ ዕድል ይከፍታል >>

ጋሎችን በፀረ-እስላምነት በቀላሉ ለመመልመል ታስቦ የተጻፈው ሽንገላና ከንቱ ውዳሴ ደግሞ እንዲህ ተብሏል።
"The Gallas living South of Shoa appeared to be numerous, virile people, capable of resisting Muslims onslaughts. They are relatively unaffected by any false religious principles. In a word, they could become the " Germans" of Africa. " (ያው ገጽ 13 መግቢያ )

ባማርኛ ሲተረጎም፤

<<ከሸዋ በስተደቡብ የሚኖሩት ጋሎች ብዛት ያላቸው ይመስላል፤ የስላሞችን የመስፋፋት ወረራ ሊመክቱ የሚችሉ ብርቱ ሕዝብ ናቸው።
ባጭር አባባል የአፍሪቃ ጀርመኖች ሊሆኑ ይችላሉ።>>

የወረሞ ጠባብ ጎሠኞች ፀረ-ኢትዮጵያ ጥዋት ማታ ድግምት ዋና ምንጩ ይህ ዓይነቱ ዶሮን ሲድልሏት በመጭያኛ ጣሏት የሚሉት ነው። ጀርመኖች እንኳን ከጥቁር ወገን ሊሆኑ ቀርቶ የውሮፓ ስላቭ ዘርያ ሞስኮቦችን፣ ፖላንዶችን፣ ሰርቦችን፣ ወዘተረፈ ሰው አይደሉም ብለው ይልቁንም ያውሮፓ አይሁዲዎችንና ጅፕሲዎችን ለይተው መፍጀታቸው አይዘነጋም።

# ከኦርማኒያ ወደ "ኦሮሚያ"

ዩሐን ክራፍ ከኢትዮጵያ ከተባረረ በኃላ ባቀናበረው ሕተታ ጋሎች "ኦርማኒያ" ተብለው እንዲጠሩ ሲያቀርብ፤

" The name "Gallas" in their own language means immigrants, and has been given them by Arabs and Abessinians. They call themselves "orma " or "oroma" strong or brave men and their language they call " Afan orma," the mouth of the Ormas; so as the Gallas have no general name to indicate their nationality or its seat, I propose to include under the desigination of "Ormania" (ያው ገጽ 73 )

ትርጉሙ፣

"ጋሎች" የተባለው ቃል በራሳቸው ቋንቋ ትርጉሙ ስደተኛ ማለት ሲሆን በአረቦችና አበሾች የተሰጣቸው ነው። እራሳቸውን "ኦርማ" ወይም "ኦሮማ" ትርጉሙም ጎበዝ ሰዎች ሲሆን ቋንቋቸውንም "አፈ ኦርማ" የኦርማዎች ልሳን ይሉታል። ጋሎች ለራሳቸውና ለሚኖሩበት አጠቃላይ መጠሪያ ስለሌላቸው "ኦርማኒያ" ተብለው እንዲጠሩ ሃሳብ አቀርባለሁ።

ይሁንና የጋልኛ ቋንቋ ሊቅ የነበሩት ሌላው ጀርመናዊ ካርል ቱትሽክ የክራፍን ሃሳብ በመቃወም፣ አረቦችና አበሾች ጋላ የተባለውን ቃል ፈጣሪ እንዳልሆኑ፤ ከራሱ ከጋልኛ ልሳን የወጣ መሆኑን ሲገልጹ፣

" The Gallas recived their names from their own language and not from Abyessinians as most outhers supposed. The word is derived from the verb ***gala,*** to go home, to seek onès home and is to be brought in connection within the historical fact that the Gallas; driven by some cause or other from their homes in 1735 rushed in torrents towards Abyssinia and made this country their home." ( Karl Tuschek: Lexicon der Galla Sprache, (München:1844) P.XX)

ትርጉሙ፤

ጋሎች ስማቸውን ያገኙት ከራሳቸው ቋንቋ ነው እንጅ ብዙዎች እንደ ገመቱት ከአበሾች አይደለም። ቃሉ የወጣው ገላ ከተባለው ግስ ነው። ትርጉሙም ወደ ቤት መሄድ፣ መግባት ቤትን መፈለግ ሲሆን ይ.ህም ከታሪካዊው ሐቅ ማለት ጋሎች ከመኖሪያ ቤታቸው ከ1735 ዓ.ም በፊት በሆነ ምክንያት ተባረው ወደ አበሻ አገር እንደ ጎርፍ ገብተው መኖሪያ አገራችው ማድረጋቸው ነው።

በዚያኑ ወቅት የክራፍን ኦርማኒያ ፍልሰማ በመቃወም በደቡብና መሓል አገር ቆይተው የተመለሱት የጅኦግራፊ ባለሙያ ዶክተር ቻርልስ ቴ. ቢክ የተባሉት በሚያዚያ 25 ቀን 1845 ዓ,ም ሎንደን ላይ በተደረገው የፈላስፎች ጉባኤ ላይ
" on the countries south of Abyssinia...." (ከአበሻ በስተደቡብ ሰለሚገኙ አገሮች...)

በተስፕ ርዕስ ባቀረቡት ዘገባ ገጽ 96 ላይ ለምን አዲስ ስያሜ ያስፍልጋል? ጋላ የተባለው ቃል ዓለም አቀፋዊ ተቀባይነት ያገኘና የታወቀ ሆኖ ሳለ ሌላ ለምን አስፈለገ ብለው ተቃውሚቸውን አሰምተዋል።፣ የፈረንሳዊው ኤም ዱ አባዲ በበኩሉ የጋልኛ ቋንቋ ኢልሞርሞ ተብሎ እንዲጠራ የሰነዘረውንም ሃሳብ ውድቅ አድርገውታል።
ጥቂት የጋላ ልሂቃን ክራፍ ያወጣላቸውን ልብ ወለድ መጠሪያ ስም ኦርማንያን አሻሽለው ማለትም ኦሮሚያ ብለው፣ የኢትዮጵያን ሕዝብና መንግሥት እያሌ ሺህ ዘመናት ታሪክና ሥልጣኔ በመቶ ዓመት ብቻ ወስነው ኦሮሚያ ተብየ ትልቅ ካርታ ሥለዋል።
ጥንታዊውን የሸዋ ክፍለ ሃገር አውራጃዎች ያማራ፣ የጋፋት፤ ያርጎባና የጉራጌ እንዲሁም የሃድያ ከምባታ ምድር ሁሉ ለኦሮሚያ ተከልሏል። የሚሲዎን ምልምል ጥቁር ፈረንጆች ኢትዩጵያውያንን ልክ እንደ ባሕር ማዶ ጌቶቻቸው "አቢሲኒያንስ" እያሉ በመጥራት የቅኝ ተገዥነት በሬው ላም ወለደ ፀረ-ዐማራ ጥላቻ ያናፍሳሉ። "ጋላ ብለው የሚጠሩን ዐማሮች ናቸው" እያሉም ይወሻክታሉ። ዳሩ ግን ባማርኛ ይሁን በግእዝ ጋላ የተባለው ቃል ትርጉሙ የነገድ መጠሪያ ስም እንጂ ሌላ ትርጓሜ የለውም።
ከሁሉ በተቀዳሚም ጋላ የሚለው መጠሪያ ቃል ከሱማሊኛ ቋንቋ የወጣው ነው (የሊዎ ራይነሽ ሱማልኛ መዝገብ ቃላትን ይመለከቷል)። ትርጉሙም እስላም ያልሆነ፣ ሃይማኖት የሌለው አረመኔ፤ አእዋሚ ማለት ነው። ዛሬም የሱማሌ ነገድ ጋላን ጋላ ብሎ ነው የሚጠራው። ልዩ ልዩ

የምሥራቅ አፍሪቃ ነገዶችም በተለይም የዋስዋሂሊ ዜና መዋዕል ኪታብ አል ዛንጅ ( Kitab al-zanuj ሰፊ ታሪክ ባረብኛ የተጻፈው ጋላን ጋላ ብሎ በኑ ቀይስ ጊላን ከሚባል ነገድ የወጡ አረመኔዎች የሚገድሉትን ሰው ቁላ ሰላቢዎች መሆናቸው ተገልጿል ( Reinhardt Klein- Arendt: Undn die Araber bauten Mogadisho.. ( Marburg 2004) , pp 26 -42)

ታዲያ ኦነግና ቀጣሪዎቹ አበሻ ዐማራዎች ጋላ ብለው ስም አወጡልን እያሉ በውሸት ይቀዣብራሉ:: እራሳቸው በራሳቸው የሚሰጡትን የቃሉን ትርጉም ቀጥሎ እንመልከተው::

"Galla-uncultured " (http://www.oromoliberationfront.org/hist)

"The term Galla is loaded with negative conotation." (M. Hassen, the Oromo of Ethiopia: History 1570-1860, (Cambridge:1990) , P. Xi)

በዝቅተኝነት ስሜት ዓይነ ሕሊናቸው ታውሮ ማንነታችውን ሸፍጠዋል:: ለዘረኛ ነጮች አጨብጭፖያቢነት አድረዋል:: የኢትዩጵያን ማኅበረሰብ በተለይም የሸዋን ነባር ሕዝብ ታሪክና ስም በማጥፋትና በመወንጀል አዲስ ታሪክ ለመጻፍ እራሳቸውን ኦረሞ ብለው የሚጠሩት ጥቂት "ምሁሮች" ፀረ-ኢትዩጵያ ትርኪ ምርኪ ብብዛት አጠናቅረዋል:: የጋላ ነገድ ኢትዩጵያን ወሮ አልሠፈረም:: ዓለም ሲፈጠር የነበረ ነባር ነዋሪ ነው እያሉ ተረት ተረት ይተርካሉ:: በ "አቢሲኒያንስ" ከመቶ ዓመታት በፊት ቅኝ ግዛት ከመሆኑ በፊት "ነፃ የገዳ ዴሞክራሲያዊ ሪፓብሊክ" እንደነበረ ኦነግና ብጤዎቹ የኅጥና የጎሣ ጠበብቶች አዲስ የወረሞ ታሪክ በመፈልሰፍ ላይ ይገኛሉ::

ጥንታዊ ታሪክና ሥልጣኔ የለሾቹ የሰሜን ምዕራብ አውሮፓ የ19ኛው ክፍለ ዘመን ዘግይቶ ደረሽ ሞግዚቶቻቸው <u>የአሪያን ዘርያ</u> ተብዬ ዘረኞች ሁሉ በጎሣ ጥናት ባለሙያነት ካባ ተሸፋፍነው በአውሮፓ ሥር የሰደደውን ፀረ ሴማወያን ቅስቀሳ ለኦነግና ብጤዎቹ አገር በቀል ምልምል ያስክናሉ:: እራሳቸውን በራሳቸው ምዕራባውያን በሚል ስያሜ የነጭ ዘርያ የአሠልጣኝነት ተልእኮና የበላይነት ስሜት ያናፍሳሉ:: የአፍሪቃንና የእሲያን ሕዝብ በከፋፍለህ ግዛ ስልት ሽንሽነው ጥገኛ የማስደረግ ዓላማቸው እንዳይሰናከል በስውርና በግልጽ የሚያደርጉት ስልት ነው:: የነ ሻዕቢያና ኦነግ ወኪሎችና አፈ ቀላጢዎች ሆነው የፈጠሩትን የውሸት ታሪክና ያበሻ ሕዝብ የጥላቻ መርዛቸውን በተቀንባበረ ስልት ሲነዙ ቆይተዋል፤ ዛሬም ይነዛሉ::

ለዚህም ዓይነተኛ ምሳሌዎች ማቅረብ ቢያስፈልግ እንደ ሆልኮምብ ና ሲሳይ / የኢትዩጵያ

አፈጣጠር (The invetion of Ethiopia, 1990)፣ ጆን ሶረንሰን የኢትዩጵያ ቅርጸታ / Imaging Ethiopia, 1993 / ፣ የጣሊያናዊው አሌክሳንድሮ ችሩሊ፣ የእንግሊዙ ባስ ባክስተር፤ ሪቻርድ ግሪንፊልድ፤ የእንግሊዝና ግሪካ መጤቃው ጆን ማርካኪስ፤ ወዘተረፈ ሁሉ አፍቃሪ ፋሽሽትና ናዚዎች፣ በጎሣ ጥናትና ታሪክ ሽፋን ድብቅ ከፋፋይ ፀረ ጥቁር አሳባቸወን ለቅጥረኛ ነፃ አውጪ ግንባር ተብዬዎቹ ለነ ሻዕቢያ፣ ኦነግ፤ ትሕነግ ወዘተረፈ ሞግዚት ሆነው ሲያናፍሱ ቆይተዋል::

ለምሳሌ ዘመናዊወን የወረሞ ምሁር ዶክተር መሐመድ ሐስን በእንግሊዙ ፀረ አበሻ ግሪንፊልድ ተመልምሎ ዶክተር ለመባል ያጠናቀረውን ሐተታ The Oromo of Ethiopia: A History 1570-1860, (Cambridge: 1990) በተሰኘ ርዕስ የተጻፈወን ፀረ ኢትዩጵያ ዝባዝንኪ እንዲሁም ከግሪንፊልዳ ጋራ ተባብሮ (Interpretation of Oromo Nationalism, In Horn of Africa vol.3 No. 1980 ) መጥቀስ ይቻላል:: እንደ አሰፋ ጀለታ፤ አቢዩ ገለታ፣ መኩሪያ ቡልቻ ወዘተረፈ የመሳሰሉት አዲስ የጋላ የፈጠራ ተምኔታዊ ታሪክ፤ ባሕልና ሃይማኖት ፈልስመው ያናፋሉ:: (Http://www.oromia.com/ Articles/ Ethiopian-System-of-domination.html ,Nov.2000)

መሐመድ ሐሰን በዶክተር መባያ ሐተታ ላይ <u>በከፊል ብቻ</u> የጋሎችን ፍልሰት አምኖ የሉባ ወራሪ ጦር አዝማቾችን እነ መልባህ (1522-1530)፤ ሙዳና (1530-1538)፤ ኪሎሌ (1538-1546)፣ ወዘተረፈ. በደፈጣ ውጊያ የኢትዩጵያን አጤ መንግሥት ግዛት በጀግንነት እንደወረሩ ገድለ ውዳሴ ሲጽፍላቸው፣ የኢትዩጵያ አጤዎችን የመከላከል ጦርነት እያጥላላ፣ የፀረ ኢትዩጵያ ጌቶቹና ሞግዚቶቹ ዘወትር ማነብነብን ማለትም "የባሪያ አደንና ፍንገላ አስመስሎ" ጽፏል::

የሚያስገርመው ነገር በጋላ ወረራ ወቅት የዓይን ምስክር ሆነው ድርጊቱን የመዘገቡትን፤ ከጋሞ ሕዝብ ተወላጅ የነበሩት ከትወልድ አገራችው ከጥንታዊ ጋሞ አውራጃ በጋላ ሉባዎች ወረራና ዝርፊያ የተባረሩትን አባ ባሕርዩን እንኳን ሳይቀር ተቃወሚል (በገጽ 1 ይመልከቷል) :: አባ ባሕርይ <u>ዜናሁ ለጋላ</u> በሚል ርዕስ በግእዝ ቋንቋ በ1585 ዓ.ም ከፍተኛ የታሪክ ሰነድ መዝግበው አቆይተውናል:: ለምን አገራችን ወደመች? ብሎ በመጠየቅ አባ ባሕርይ ያቀረቡት ሰፊ ማኅበረሰባዊ ትንታኔ ፍጹም ወደር አይገኝለትም::

በሌላ በኩል ደግሞ ከመረቁ አወጡልኝ ከሥጋወ ጠመኛ ነኝ እንዲሉ የጋላ ጠባቦችና የጎሣ ነፃ አውጭ ነን ባዩች ሁሉ ሰለጋላ ነገድ በአባ ባሕርይና ሌሎች ኢትዩጵያወያን የተጻፈወን <u>መልካም ነገር ብቻ</u> ዘወትር መጥቀስ ሲወዱ በአንጻሩ ስለ የሉባ የየስምንት ዓመት በጎረቤት አገር ሕዝብ ላይ የደፈጣ ጦር ወረራና <u>ቁላ ቆራጭነት፣ ጨካኝ አረመኔነት</u> እንዳይታወቅ በመመኘት "ያቢሲኒያንስ ደብተሮችን ታሪክ ጸሐፊነት አንቀበልም"

እያሉ የኦነግ ካድሬዎች ቡራ ከረዩ ይላሉ። ፈረንጅ አምላካቸው ብቻ የሚላቸውን ሰምተው እንደ በቀቀን ተግተው ያስተጋባሉ። ነገር ግን ከአበሻዎች ሌላ ያውም በቅርቡ ያውሮፓና እሲያ ስለ ጋላ ሉባ ሰላቢነት የጻፉትን ቀጥሎ ያገነዘቧል።

<< The gada System of the Boran provided the rule that each new set initiated into the raaba grade had to go on a rituasl war expidation to procure livestock and the cut off genetials of a male strangers as trophies. As these initiations took place every eight years, the neighbours of the Boran were subjected to a reign of periodic terror. >> (Eisei Kurimoto, Simon Simones: *Conflict, Age & power in North East Africa* 1998, p128)

እንዲሁም የምሥራቅ አፍሪቃ ዋስዋሂሊ በአረብኛ ቋንቋ የተጻፈው ዜና መዋዕል (የጥቁሮች መጽሕፍ-ኪታብ አል ዛንጂ) አረቦች ሞቃዲሾን መሠረቷት (Und die Araber bauten Mogadishu) በሚል ርእስ ራይንሃርድ ክላይን አረንደት እ.አ.አ 2004 ጋሎች ከአረቢያ የመን እንደመጡና አእዋሚ መሆናቸውንና የጠላታቸውን ቁላ ሰልበው ካላሳዩ በስተቀር ሚስት ማግባት እንደማይችሉ በጀርመንኛ ቋንቋ በተጻፈው መጽሕፍ ገጽ 40 ላይ የሰፈረውን ያገናዝቧል። ከሁሉም በላይ ደግሞ ያይን ምስክሮቹ አነ አባ ባሕርይና የፖርቱጋል ኢየሱሳውያን ሚስዮኖች አነ አባ ጀሮም ሎቦ (1595-1678) አባ ማኑኤል አልሜዳ (1580-1646) ስለ ጋሎች በሰፊው መዝግበዋል። ለምሳሌ አባ ጀሮም እንዲህ ብለዋል።

"..... Through all these fatigues we at length came to Jubo, a kingdom of considerable extent..

I stayed here some time to inform my self wheter I might, by pursuing this road, reach Abyssinia; and could get no other intellegence but that **two thosand Gallas** ( the same people who inhabited Melinda) had encamped about three league from Jubo; that they had been induced to fix in that place by the plenty of provisions they found there. These **Gallas lay everything which they come in ruin, putting all to the sword without distinction of age or sey; which barbarities, though their numbers are not great, have spread the terror of them over all the country.** They choose a king, whom they call Lubo; every eightyear. They carry their wives with them, and expose their children without any tenderness in woods, itbeing prohibited, on pain of death, to take any care of those which are born in the comp...... They feed upon raw cow's flesh; when they kill a cow they keep the blood to rub their bodies with and wear the the guts about their necks for ornaments, which they afterwards give to their wives. ( A voyage to Abyssinia: By father Jerome Lobo, Chapter II, 1789)

በኢትዮጵያ ጥንታዊ አገርነትና የጥቁር ሕዝብ ሥልጣኔ ለሚቀኑ ዘረኞች ስውር ሴራ አራማጅነት ተቀጥረዋል። በተጨማሪም መሐመድ ሐሰን በአፍሪቃ አህጉር ምደረ አበሻ የኢትዮጵያ ግእዝ ፊደልና ሥነ ጽሑፍ መኖር ምክንያት ጌቶቹ በቅናትና ጥቁር ጥላቻ ያጠናቀሩትን መልሶ ከፍ ብሎ በተጠቀሰው መጽሐፉ ሲያቀነቅን፣

" ... They ("Abyssinians") played down their Africaness. Christian and Negro were often cited as opposite, as good and evile. Oromo or Galla as it was called, derived from Africa.." (ገጽ 3)

ትርጉም፣

<< አበሾች ጥቁር አፍሪቃዊነታቸውን አይቀበሉትም። ክርስትናና ሻንቅላነት እንዲሁም ጽድቅና ኃጢአት በተቃራኒነት ዘወትር ይጠቅሳሉ። ጋላ ከጥቁር አፍሪቃ የተገኘ ነው።>>

ይህማ ምነም አዲስ ግኝት ሳይሆን ዠሯችንን እጅግ በጣም ያሰለቸው ዘረኛ ነጮች የጥቁር ሕዝብ ወገንን ሁሉ በዓለም ዙሪያ በብቸኛይቱ ነፃ የጥቁር ሕዝብ መንግሥትና ምሳሌነት እንዳይኮሩና ፀረ ቅኝ ግዛት ትግላቸውን አጋር ለማሳጣት ያቀናበሩት ስብከት ነው። መሓመድ ሐሰን የሸፈጠው የርሱ ወገኖች የሐረርጌ ቆቱዎች ልክ እንደ ሱማሌዎች አረብ ነን የአረብ ዘርያዎች የነቢዩ ዘመዶች ነን እንጅ መቼ ጥቅር አፍሪካውያን ይላሉ። አይካ ሃበርላንድ ባደረገው የመስክ ጥናት ቆቱዎች እርሳቸውን እስላማ እንጂ ኦሮሞ ተብሎ መጠራትን በፍጹም አይፈልጉም። ኦሮሞ ማለት አረመኔነት

አእዋሚነት ሰለሚመስላቸው ነው በማለት ገልጾታል። መሐመድ ሐሰንም ሆነ ብጤዎቹ የአረብኛ ስም የወረሱት አረብ ነን ወይም እንሁን ብሎው ነው። የጋላ ልሂቃን ከፋሽስቶችና ከፀረ ጥቁር ዘረኞች የሰሙትን ማስተጋባት ዝቃጭነት ነው። ኢትዩጵያ በዓለ ላይ በቸኛ ነፃ የጥቁር ሕዝብ አገር በመሆኗ አይደለም እንዴ ጥቁር አሜሪካውያን በኒዩርክ፣ በፊላደልፊያ፣ ወዘተረፈ ሰላማዊ ሰልፍ ወጥተው የአረመኔ ፋሽስት ጣሊያንን ወረራ የተቃወሙት፤ ጥቂቶችም በቀጥታ ወደ ኢትዩጵያ መጥተው በጦር ግንባር ተሰልፈው የተዋጉት? እነ ከዋሚ ንክሩማ፤ ጆሞ ኬኒያታ፤ ኢዚክዌ፤ ማርቆስ ጋርቬ ወዘተረፈ ኢትዩጵያን በመደገፍ ሲንቀሳቀሱ የነበሩት? እንኳን ጥቁሮች በዓለም ዙሪያ ይቅርና ቀዩች፣ ብጪያዎችና ነጮችም ጭምር ኢትዩጵያን በመርዳት ተባብረዋል።
የሐረርጌ ቆቱ መሓመድ ሐሰንን ያበሻ ጥላቻ ያስካነው ሪቻርድ ግሪንፊልድ ነው። ይኸ ሰውና ጆን ማርካኪስ የተባለው ቀኃሥ ዩንቨርስቲ አስተማሪ ነን ብለው ተማሪዎችን በፀረ ኢትይጵያ ቅስቀሳ ሲደረራጁ ተጋልጠው ከተባረሩ በኋላ አንዴዬ ሱዳን ሌላ ጊዜ ሱማሊያ፤ ኬኒያ፤ ናይጀሪያ ወዘተረፈ መሽገው ዘወትር ፀረ ኢትዩጵያ ዘመቻ አድርገዋል። ግሪንፊልድ ሳይሞት የኤርትራ መገንጠል ተሳክቶለት አስመራ ሮጦ ገብቶ ከቆዬ በኋላ ድብን ብሏል። ማርካኪስ ግን ኢትዩጵያ ብቻ ሳትሆን መላው ጥቁር አፍሪቃ በጎሣ ተሸንሽኖ መንግሥት እንዲመሠረት ላይ ታች ያዳክራል። አሁን ደንበኛነቱን ከኦነግ፤ ከትሕነግና ተለጣፊ አጋሮቹ ጋራ ማድረጉ ታውቋል።

## <u>በኢትዩጵያ ባሪያ ፈንጋይና ነጋዴዎች እነማን ነበሩ?</u>

በኢትዩጵያ ከጥንት ጀምሮ የክርስቲያን ልጅን ለባርነት የሸጠና ያሸጠ ክርስቲያን ዜጋ በፍትሐ ነገሥት የሞት ፍርድ በስቅላት ይፈረድበት እንደነበረ እነክራፍ ሸፈጠዋል። በገብር አልገብርም የሥልጣን ሽሚያ ጦርነት የሚማረኩትን ሁሉ "ባሪያ" አድርገው ቆጠረዋቸዋል። ነገር ግን በአገራችንም ሆነ ሌሎች አገሮች የጦር ምርኮኞች ሁሉ በነገሥታቱና መኳንንቱ ቤት ክርስትና ተነስተው፣ የቤተሰቡ አባል ሆነው ከልጅና ሥጋ ዘመድ እኩል እንደ ሥራቸውና አገልግሎታቸው መጠንና ትጋት ቤትና ንብረት፣ ርስት እንኳ ሳይቀር ይወርሱ እንደ ነበር የተረጋገጠ ነው።
መቸም ፈረንጆች በጅምላ ዋሾችና ዘረኞች፣ አጭበርባሪና ጉረኞች አይደሉም። እንደ ሄንሪ ሶልትና ጆን ከምዴን የመሳሰሉትን ሐቀኞቹ በትክክል ያዩትንና የሰሙትን መዝግበዋል።
በ19ኛው ምዕተ ዓመት መጀመሪያ ገደማ ሄንሪ ሶልት የተባሉት ኢትዩጵያን ጎብኝተው ስለባሪያ ንግድ ሁኔታ ቀጥሎ ያለውን መዝግበዋል።

The situation of slaves is rather honourabel than disgraceful and the difference between their state and that of western slaves is strictly apparent. They have no long voyage to make, no violent change of habits to undergo, no outdoor labour to perform, no white mans scorn to endure, but on the contrary are frequenly adopted like children into the family. (Salt, 1814 p.382)

ባማርኛ ሲመልስ፣

የባሮች ሁኔታ የሚያሳፍር ሳይሆን የሚይስክብር ነው። በምዕራቡ ዓለም ከሚገኙት የባሮች ሁኔታ በፍጹም የተለየ ነው። ትልቅ ጉዞ የለባቸውም፣ ልማዳቸውን በኃይል ለማስለወጥ አይገደዱም፣ ከቤት ውጪ ሥራ የለባቸውም፣ የነጭ ሰውን ቁጣና ግልምጭያ ተሸካሚ አይደሉም፣ በተቃራኒው እንዲያውም አብዛኛውን ጊዜ እንደ ጉዲፈቻ ሕፃናት የቤተሰብ አባላት ይደረጋሉ።
አዎ! በመላው አፍሪቃ የባሪያ ንግድ ተደርጓል። በሰሜንና ምሥራቅ ከግብፅ እስከ ሞዛምቢክ ድረስ በጠረፍ ዳርቾች ለምሳሌ ምጽዋ፣ ታጁራ፣ ዘይላ፣ በርበራ፣ መቃዲሾ፣ ማሊንዲ ሞምባሳ፣ ዛንዚባር፣ ዳረሰላም ወዘተረፈ, ለቱርክና አረብ ባሪያ ገባያ ማቅረቢያ ጣቢያዎች ነበሩ። ነጋዴዎቹም ይሁዲዎች፤ አረቦችና የአካባቢው ተወላጅ እስላሞች እንደነበሩ የተረጋገጥእ ነው። <u>ጀብርቲ</u>ና ውርጂ ተብለው የሚጠሩት ነጋዴዎች በመላው አፍሪቃ ነግደዋል። ጀበርቲዎች ያረብ ክልሶች ሲሆኑ በሐረር፣ በታጁራ፣ ዘይላና በርባራ ሰፍረው ነበር። በአፍሪቃ ቀንድ የጀበርቲዎች ታሪክ ከ11ኛው ክፍለ ዘመን ሼህ ኢስማኤል ጀበርቲ የዳሮድ ሱማሌ ጎሣ ቅድማያት ከአረብያ ፈልሶ ሰሜን ምሥራቅ ሱማሌ ሰፍሯል። በአፍሪቃ ቀንድ ሰሜንና ምሥራቅ ጀበርቴዎች የባሪያ ንግድ ገበያውን በብቸኛነት ይዘው ያለምንም ችግር ለግብፅና አረቢያ እንዲሁም ለፋርስ ባሪያ አቅራቢዎች ነበሩ። የባሪያ ንግዱም በአብዛኛው ሕፃናትን በተለይም ልጃገረዶችን ይመለክታል። ሕፃናቱ የሚመጡበት አካባቢ ደቡብና ደቡብ ምዕራብ ኢትዩጵያ ሲሆን የጋላና ሲዳማዎች አባቆሮዎች እነዚህን ሕፃናት የሚያገኙት ደካማ ከሆኑ ጎረቤቶቻቸውና በመካከላቸው ባለው ጦርነት፣ ባሪያ ፍንገላና አደን እንደነበረ የፒ ኢ ለቭጆይ ጥናት ያረጋግጣል።
ይህም፣

" The slave trade was largly a trade in children especially girls. The children were brought from regions south and Southwestern Ethiopia. The Galla and Sidama principalities obtained many of these children in slave raids on their weaker neighbours or in disputes between themselves. Many were kidnapped and some were purchased in times of famine. A distinction was made between the "red" and " "black" slaves." (P.E Lovjoy; *Transformation in Slavery; Cambridge: 1983, pp.149-150*)

**ቀደም ሲል ጆን ኮምዴን የተባሉት** " Abyssinia and its people " (**ኑሮ በቄስ ዩሐንስ አገር**) **እ.አ.አ በ1868 ዓ.ም በለንደን ከተማ ባሳተሙት መጻሐፋቸወ ገጽ 194 ላይ የሚከተለውን አስፍረዋል።**

" The slave trade is carried on by the **<u>Mohamedans</u>** alone. Chrstians buy for domestic purpose, but are not permitted to sell, and the penality of death by hanging is affixed to the act of selling a christian child. The Gallas are solled by their despotic kings in the territories of Enarea and Djimma."

ባማርኛ ሲመለስ፣

"የባሪያ ንግድ የሚከናወነው በእስላሞች ነው። ክርስቲያኖች ለቤት አገልግሎት የገዛሉ ለመሸጥ ግን አይፈቀድላቸውም። የክርስቲያን ልጅ የሸጠ ቅጣቱ ስቅላት ነው። ጋሎች የሚሸጡት በፈላጭ ቆራጭ ንጉሣቸው በጅማና እናሪያ ግዛት ነው።

" The southern most provinces of Galla, Enarea, Djimma, Goma and others are governed despotically by their several chiefs and supply by arbitrary coercion slaves for the Turkish market . "

ትርጉሙ፣
" በደቡብ ዳር የጋላ ክፍለ አገሮች እንደ እናሪያ፣ ጅማ፣ ጎማና ሌሎቹም የሚግዙት በፈላጭ ቆራጭ አባቆሮዎቻቸ ሲሆን እያስገደዱም ለቱርክ የባሪያ ገባያ አቅራቢዎች ናቸው። "

ኮምዴን ዘገባቸውን ቀጥለው በገጽ 201 ላይ የሠፈረው፣

**" The Gallas of a district named Follo pay a heavy tax to the king of Djimma, for the permission to purchase boys and prepare them as eunuchs for the Turkish harmes."**

ባማርኛ፣

" በፎሌ ወረዳ የሚኖሩት ጋሎች ወንድ ልጆችን እየሰለቡ ማለት ጃንደረባ እያደረጉ ለቱርክ ገበያ ለማቅረብ ፈቃድ ለማግኘት ለጅማው ንጉሥ ከባድ ግብር ይከፍላሉ። "

በደቡብና ምሥራቅ ኢትዩጵያ ከዛሬ መቶ ሃምሳ ዓመት በፊት የነበረውን እጅግ በጣም ዘግናኝ ሁኔታ ከፍ ብሎ ሐቀኞቹ የመዘገቡትን ስናገናዝብ፤ ዛሬ አንዳንድ ግለሰቦችና "የጎሣ ነፃ አውጭ ግንባር" ነንባዩችን ፀረ ዐማራ መቀዣበርን ከሥር መሠረቱ ለማጋለጥ እንሆ ያለምንም ይሉኝታ ሐቁን ለማወቅ ዕድል ሳልገጠማቸው ወገኖቻችን ለማሳወቅ መንፈሳችን በከፍተኛ ትጋት ይነሳሳል።

የሸዋው ዐማራው አጤ ምኒልክ " መሬታችንን ቀማን፣ የገዳ ባሕላችንን አጠፉብን፣" <u>ዴሞክራሲያዊው የገዳ ሥርዓት</u>" እድገቱ ተጨናገፈብን፣ የነፍጠኞች " ባሪያ" ተደረግን ወዘተረፈ. እያለ በሬው ሳም ወለደ ተረት ተረት አነግ ተብዬው አረመኔ ወንጀለኛ ቡድን የውሸት እምቢልታውን ይነፋል። አጋጣሚ ሁኔታዎችን በመጠቀም ፀረ ዐማራ ዘመቻን በያለበት በማድረግ ብዙኃን ዐማራዎች በአሶሳ፣ በበደኖ፣ በአርባጉጉ በነኦነግ ተጨፍጭፎዋል፤ ተፈናቅለዋል። በጥቁር ሕዝብ ጠላቶችና በፀረ-ኢትዩጵያዊነት ስብከትና ቅስቀሳ ተግተውና ተክነው ሳይና ታች የሚሉ ቅጥረኞች አደብ እንዲገዙ በአፅንኦት እናስጠነቅቃለን። ወደ ሕሊናቸው ተመልሰው ማስተዋል ይችሉ ዘንድ ሐቁ ከለይ በዝርዝር ቀርቦላቸዋል። ዐማራው ማኅበረሰብ እራሱን ለመከላከል፣ የተቃጣበትን ጥቃት መክቶ ጥላቶቹን ድባቅ ለመምታት አቅምና ብቃት አለው። ይህ ሊታወቅ ይገባል። እስከዛሬም ይህ ጥቃትና በደል የተፈጸመው ዐማራውን በውሸት ኢትጵያዊነትና አድነት ሽፉን የሥልጣን ጥመኞች በዐማራነቱ እንዳይደራጅ ዘወትር በሚያደርጉት ሴራ ነው።
የባሪያ ሥርዓት በኢትዩጵያ ብቻ ሳይሆን በሌላው ዓለም እንደነበረው ሁሉ ከአክሱም መንግሥት ዘመን በፊትም ሆነ ኋላ ነበር። በመካከለኛው ዘመን ይልቁንም

በደቡብ፣ በመሓልና ምሥራቅ ኢትዮጵያ ክፍለ ሀገራት በይፋት፣ በሃድያ፣ በባሌ፣ በዘይላ፣ በአዳል፣ በደዋሮ (ሐረርጌ) ወዘተ እስላማዊ ሡልጣናት እንዲሁም በአእማዊዎቹ የጅንጃሮ፣ የሱጋሞ፣ የዳሞት፣ የጎንጋ ወዘተ. ማኅበረሰብ ባሪያ ፈንጋዮች ነበሩ። ይህንንም ሁኔታ ታዋቂ የአረብ የጅኦግራፊና የታሪክ ሊቃውንት እነ እድሪስ ኢበን ሀኩል፣ ማሱዲ፣ ኢበን ባቱታ፣ ማቅሪዝ ወዘተ. በሰፊው መዝግበውታል። በተለይም ኦልማሪ (በ1335ዓ.ም)፣ ማቅሪዝ (በ1430ዓ.ም) የመካከለኛው ዘመን የኢትዮጵያ እስላማዊ ግዛቶችን ማለት የሃድያን፣ የደዋሮን፣ የአራባቢኒ፣ የይፋት፣ የሸርካ፣ የአዳል ዘይላን አስመልክተው በተለይ ደግሞ በሃድያ ሡልጣን ብዙ ባሮች ከየቦታው እንደሚወሰዱና ጀንደረባ ተደርገው በዘይላ ወደብ በኩል ለአረብ ገበያ ይልኩ እንደነበረ ተመዝግቧል። <u>ወሸሉ</u> ከተባለ ቦታ እየተሰለቡ ለገበያ ይቀርቡ እንደነበረ በጀርመንኛ የተደረገውን ጥናት ያገናዝቧል፣

Nach Hadija stroemen sehr viele Sklaven und Eunuch zusammen. Verschnitten wurden aber in der Stadt ***<u>Washellu</u>*** gemacht, da dies in Abeessinien verboten sei, und Washelu die einzige Stadt sei, wo dies geschehen duerfe. (P.Paulischke Adal-Laender 1884 Leipzig, p.17) ባማርኛ፣

አያሌ ስልብ ወይም ጀንደረባዎች ወደ ሃድያ ይጎርፋሉ። የሚሰለቡት ግን በወሸሉ ከተማ ነው፣ በአበሾች ዘንድ የተከለከል ስለሆነ በወሸሉ ብቻ ነው ይህ ድርጊት ሊከናወን የሚቻለው።
የይፋት ወላስማዎች ከሸዋ ወደ አውሳና ሐረር ተዛውረው በ1445 ዓ.ም ሐረርን ቆርቁረው የባሪያ መነገጃ ዋና ማዕከል አድርገው ለኢትዮጵያ አጤ መንግሥት ሳያመቻቸው እየገበሩ፣ ሲመቻቸው እያመጹ የሃይማኖት ጦርነት ጅሃድ ሲያካሂዱ እንደነበረ ይታወቃል። በተለይ ባጤ ልብነ ድንግል (ወናግ ሰገድ) ዘመነ መንግሥት (1508-1540) ግራኝ አህመድ ተነስቶ ዋና ማዕከሉን ደምቢያ አድርጎ ከፈተኛ እልቂትና የባሕል ውድመት ማድረጉ በአረብ ፋቂ በትክክል ተመዝግቧል።
በ1559 ዓ.ም አጤ ገላውዴዎስ በዛሬው ጨርጨርና ጋራጉራቻ አውራጃ ከዓሊ ኑር መሐመድ ሠራዊት ጋራ በተደረገው ጦርነት ከተገደሉና ከተከታዩም የባረንቱ ወረሞ (ጋላ) ወረራ በኋላ እስከ 1887 ዓ.ም ድረስ ሐረር የአዳል ወላስማዎች ዋና ከተማ ለአረብና ለቱርክ ባሪያ ማቅረቢያ ማዕከል ነበረች። ዛሬ እራሳቸውን ሐረሬ ባዩችም የቱርክና የግብጽ ገዥዎቻቸው አሽከሮችና ተላላኪዎች ነበሩ እንጂ እራሳቸውን በራሳቸው የሚያስተዳድሩ "ነፃ ሕዝብ" በጭራሽ አልነበሩም።
ታዲያ! አንዳንድ የቆቱ፣ የውጋዴንና የአደሬ የግብጽና አረብ ቅጥረኞች ሐቁን ሸፍጠው ፀረ-ዐማራ በተለይም ፀረ-ምንይልክ ወሬና አሉባልታ እየቦተለኩ ቡራ ከረዩ ማለት ምን ይሉታል!

ከዳግማዊ አጤ ምንይልክ ዘመን ሁለት መቶ ዓመት አስቀድሞ አገራችንን <u>በሉባ</u> የደፈጣ ጦር ከባሌ እስከ ትግሬ ክፍለ ሀገራት ድረስ ያወደሙት የጋላ ልዩ ልዩ ነገድ ዘላኖች መሆናቸውን ስለምን ይሸፈጣሉ? ጥቂት አደሬዎችና ቆቱዎች የወያኔ ሻእቢያ አፓርታይድ የጎሣ ፖለቲካ ተዋኒያን አሸንጓሊት ሆነው ላይ ታች ያሸቃብጣሉ።
ከጋላ ባረንቱ ልዩ ልዩ ጎሣዎች የሉባ ወራሪ ጦር እራሳቸውን ለመከላከል ያልቻሉት የሐረርጌ የአዳል ወላስማ ሱልጣናት በሐረር ከተማ ብቻ ተወስነው መከላከያ ጀጎል ገንብተው ኋላም የቱርክና የግብፅ ቅኝገዥዎችና ተስፋፊዎች አሽከርና ተላላኪ ባሮች ነበሩ። ግብፃውያንና ቱርኮች በእስልምና ሃይማኖት ሽፋን "ወዳጅ" ኢትዮጵያውያን አጤዎች ኦርቶዶክስ ክርስቲያን በመሆናቸው ብቻ "ተስፋፊና ቅኝ ገዥ" ሊሆኑ ወይም ሊባሉ በፍጹም የማይቻል መሆኑን የሱማሌ፣ የቆቱና አደሬ ፀረ ክርስቲን ቅጥረኞች ይገንዘቡ። ሐረርጌ እስከ ዘይላ በርበራ ሕንድ ውቅያኖስ ጠረፍ ዳርቻ ድረስ የኢትይጵያ መንግሥት ግዛት ምድር ነው።
ዳግማዊ አጤ ምንይልክ በምሥራቅ ይሁን በደቡብ ምዕራብ የጥንት ኢትዮጵያን ክፍለ ሀገራት በምሥራቅ የአዳልና የደዋሮን (ምዕራብ ሕረርጌን)፣ ባሌን፣ ሃድያ ከምባታን፣ እናሪያ (ከፋ ኢሉባቦር)፣ ዳሞት (ወለጋ)፣ ፈጠጋር (አሩሲ)፣ ወዘተረፈ. በከፊል ለማስመለስ ያደረጉትን ተገቢ ዘመቻ በተለይ የኦነግ ጀሌዎች "የገዳ ዴሞክራሲዊ ሥርዓትን" ለማጥፋት የተደረገ መስፋፋት ነው እያሉ ይቀሳፍታሉ። በእርግጥ ተስፋፊውና ወራሪውማ የጋላ ልዩ ልዩ ጎሣዎችና አዝማቻቸው የሉባ ደፈጣ ተዋጊዎች፤ ዘራፊዎችና ቁላ ቆራጭ ሰላቢዎች ነበሩ።
የዘላን ማኅበረሰብ ሥርዓት የነበረው የገዳ ሥርዓት የጋላ ነገድ ብቻ ልዩ ባሕል ሳይሆን የሌሎች አያሌ የምሥራቅ አፍሪቃ ነገዶች የባንቱና አባያውን (ናይሎቲካዊ) ልዩ ልዩ ነገዶች ለምሳሌ እንደ መሳያ፣ ኮንሱ፣ ረንደሌ፣ ጊኩኩዩ፣ ረሻት፤ ናይሎቲካዊ ነገዶች ወዘተ ሁሉ የገዳ ሥርዓት ነበራቸው።
የገዳ የዘላን ጎሣ አስተዳደር ሴቶችን አግላይ፤ በወንድ ፆታና በእድሜ ቡድን ላይ የተመሠረተ ነበር። በየስምንት ዓመቱ አዲስ የጦር አዝማች ሉባ መሰየም ዲሞክራሲያዊ

ሥርዓተ ማኅበር አያሰኝም። ገዳ መክሰም የጀመረውም አስቀድሞ ነገደ ጋላ ከባሌ ማዶ ከደቡብ ሱማሌ ቤናድርና ጁባ ሸለቆ ሲባረር ከብቱን ይዞ በተከታታይ የመስፋፋት ወረራ በለምለሙ የአበሻ ምድር ላይ ሲሰፍርና <u>ከዘላንነት ወደ ግብርና ሥራ</u> ሲሰማራ ነበር እንጂ በኢትይጵያ ነገሥታት በነአጤ ቴዎድሮስ፤ በአጤ ዩሐንስና በአጤ ምኒልክ ዘመናትስ እንዳልነበረ የሕብረትሰብ እድገት ሂደት ያረጋግጣል። አይካ ሃበርላንድ ያደረገው የመስክ ጥናት ያስረዳል።

የጋላን ሕዝብ እንወክላላን ባይ ልዩ ልዩ ቡድኖች ከወታደራዊ ደርግ ጋራ ወግነው፤ በአዋጅ ኦሮሞ ተብለን እንጠራ ብለው፤ ዐማራውን ለይተው በአብዩት ሶሻሊዝም ከለላ ሲገድሉ፤ ሲያስግድሉ ቆይተው፤ አረመኔው ነፍሰ ገዳይ መንግሥቱ ኃይለ ማርያም ጓዙን ጠቅልሎ በመፈርጠጥ ዚምባብዌ ሲገባ እነ ኦነግ ከወያኔ ትግሬና ሻዕቢያ ጋራ ተመሳጥረው የውክልና ሥልጣናቸውን በአቋራጭ በኢትዩጵያ ላይ አረጋግጠዋል። ሁለት ሦስተኛውን የኢትዩጵያ ቆዳ ስፋት "ኦሮሚያ" የሚል ስያሜ በመስጠት አዲስ ነፃ አገር ለመመሥረት ደፋ ቀና እያሉ ናቸው። ወታደራዊ ደርግ በሕዝብ ጥላቻ ሲገረሰስ ኦነግ ና ወያኔ-ሻዕቢያ ዐማርኛ ተናጋሪውን ብዙኃን ኢትዩጵያዊ ሕዝብ አግልለው አገሪቱን በባንቱስታን አፓርታይድ የጎሣ ክልል ሸንሽነው፣ የሽግግር መንግሥት መሥርተዋል። ኦነግ ለተወሰነ ጊዜ የወያኔን ሥልጣን በማደላደል ረገድ ከፍተኛ ሚና ተጨያውቷል። ሆኖም በተፈጠረው ሹክቻው ተሸንፎ ቢባረርም እንኳ በሽግግሩ ወቅት ያስጀመረው ሁኔታ እንዲቀጥል የሚፈልጉ የተበታተኑ ቡድን አባላት እንዳሉት አይካድም።
በአገር ቤትና በውጪ የወያኔ ኢሕአዴግ ተቃዋሚ ነን ባይ ቡድኖች የባንቱስታን የጎሳ ፌደራሊዝም እንዲቀጥል፣ የመሬትን የግል ባለሃብትነት በኢትዩጵያ እንዳይኖር ይፈልጋሉ። ለሙን መሬት ለውጪ ከበርቴዎች፣ ለሕንዶች፣ ለአረቦችና ፈረንጆች ወዘተረፈ በያለበት በርካሽ ሲቸበችቡ ዐማራውን አነስተኛ ገበሬ ከኖረበት ይዞታው በጎሳ ማጽዳት ዘመቻ ያፈናቅሉታል።

በኢትዩጵያ የባንቱስታን የጎሳ ፓለቲካ ዋና ባለሥልጣናት የሆኑት የኦህዴድና የኦነግ ጀሌዎች እነ ሐሰን ዓሊ አማራውን ሕዝበ ክርስቲያን ለይተው ለማስጠፋት በብደኖ፣ በወተር፣ በአሰቦት፣ በድሬዳዋ፤ በአርባ ጉጉ፤ በባሌ፣ በወለጋ፤ ወዘተረፈ አረመኔ ጭጭጨፋ ማስደረጋቸው አይዘነጋም።
በዘመነ ወያኔ ኢሕአዴግ በሁሉም ከተማዎች ለምሳሌ በሐረር፣ በድሬደዋ፣ በጅጅጋ፣ በጎባ፣ በናዝሬት፣ በአሰላ ወዘተረፈ. ዐማራው ወገን ባእድና ሁለተኛ ዜጋ ተደርጎ ለአፓርታይድ የጎሣ ፖለቲካ ዒላማ ተዳርጓል።
በዐማራ ክልል ተብዬው ቁጥር 3 ውስጥ የሚኖሩት ጎሳዎች ልዩ ዞን ሲኖራቸው ብዙኃን ያማራ ተወላጆች ግን በናዝሬት፣ በሐረር፣ በአሩሱ፣ በደቡብ፣ በምዕራብ፣ ወዘተረፈ ዞን የላቸውም።
ከዚህም ሌላ የሸዋ ጥንታዊ ወረዳዎች እንደ ግንደበረት፣ የመናገሻ (እንደግብጣን) የመራቤቴ ደራ፣ የተጉለት ወግዳ፤ የሰላሌ የያ ጉለሌ፣ የሰንዳፉ፣ የቅምብቢት የደብረ ሊባኖስ፣፤ የየረርና ከረዩ፣፣ የፈንታሌ መተሃራ፣ የዝዋይ፣፣ የይፋት አጋም በር የአርጎባና ዐማራ ነባር ሕዝብ ምድር ለአፋርና ኦሮሚያ ተብዬ የፈጠራ ክልል ተከልለው ባማራና አርጎባ ነባር ሕዝብ ላይ ከፍተኛ በደል በወያኔ ኢሕአደግ ካድሬዎች ይፈጽማል። የሸዋን ሕዝብ ልክ እንደ ፋሽስት ጣሊያን ወረራ ዘመን የተደረገው ሸንሽኖና ክለላ የደረሰው ያስተዳደር በድል ከፍተኛ ነው። ያማርኛ ተናጋሪውን ስምምነትና ፈቃድ ያላገነዘበው ሸንሸና በወረዳዎች ውስጥ የሚኖሩት ያማራ ልጆች በቁቢ ፊደል ተማሩ ተብለው ጥቁር ፈረንጅ ተደረገዋል። የሸዋ ሕዝብ ሰፋፊ መሬቶች በሁሉም ስፍራ በተለይም በታችኛው አዋሽ ሸለቆ ምድረ ይፋት ከነባሩ ያማራና አርጎባ ሕዝብ ተወስዶ የአፋር ክልል የተባለው ምድር ለግብፅና የአረብ ከበርቴዎች ተሸጧል።

እነ ፕሮፌሰር አዩ ሞሚና ይማም፣ ዶክተር ገብሬ ጉልቱ፣ ዶክተር የውብዳር ዘለቀ፣ ዶክተር ገለበው ሰንገጎ፣ ገሞራው ማንያዘዋል

ይቀጥላል..............................................................................

## በክፍል ሁለት ወራሪውና መጤ ስፋሪው ማነው?